# የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ
# መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 263/2013

የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 205/2013ን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 263/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡፡፡

## 2. ማሻሻያ

የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 205/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተሰርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተተክተዋል፤

**"2/ የወጪ ማስመከሪያ**

ሀ) በአገር ወስጥ ገንዘብ ለሚፈፀሙ ክፍያዎች የወጪ ማስማስከሪያ መሂ/7/ በሣጥን የሚከናወን ክፍያ መሂ7/1፣ በባንክ በኩል የሚከናወን ክፍያ መሂ7/2 ወይም በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ዘዴ ማስተናገድ፣

ለ) በውጭ ምንዛሪ ለሚከናወን ወጪ የውጭ ምንዛሪ የወጪ ማስማስከሪያ መሂ/8/ በተፈቀደ ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ፤

ሐ) በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በሆስፒታሎች በፍርድ ቤቶች በመሂ/185 እና በመሂ/85 ከተሰበሰበው ገንዘብ ወደ ሚደበኛ ገቢ ለማዘወርና ልዩነቱን ተመላሽ ለማድረግ በቅድሚያ በመሂ/186 እና ወመሂ/86 ምዝገባና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመመዝገብ ምዝገባወን ማወራረስ፣"

2. የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5)፣ (6) እና (10) ተሰርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4)፣(5)፣(6) እና (10) ተተክተዋል፤

"4/ **የሂሣብ ምዝገባ ማዛዣ**

ጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቀስባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ሜቾቸውም የሂሣብ ክንዉኖች በሂሣብ ማዝገባ ማዛዣ ሞ/9 ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የምዝገባ ማዛዣ ሚፀም አለባቸው

5/ **የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ**

በየዕለቱ የተሰበሰበ ገንዘብ በገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ ሞ/64 ተጠቃሎ ወይም ከሞ/1 ወደ ሞ/64 በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በማጠቃለል ገቢ መደረግ አለበት፡፡

6/ **በገቢ ማለያ ቁጥር የተለየ የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ**

በገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ ጥሬ ገንዘብ የገቢ ማለያ ቁጥር የተለየ የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ ሞ/65 ተዘርዝሮ ለዋና ገንዘብ ያዥ በሞ/64 እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ጭምር መተላለፍ አለበት፡፡

10/ የመንግሥት መሥሪያቤቶች ወርሃዊ የሂሣብ ሪፖርቶችን በአገር ወስጥ ገቢ/እርዳታ/ የብድር ሂሣብ ሞ/21፣ መደበኛ በጀት ወጪ ሂሣብ ሪፖርት ሞ/22፣ በካፒታል በጀት ወጪ ሂሣብ ሪፖርት ሞ/23፣ በገንዘብ ዝወውር ሂሣብ ሪፖርት ክፍል 1 እና 2 ሞ/24፣ በተሰብሳቢ ሂሣቦች ሞ/25፣ በተከፋይ ሂሣብ ሪፖርት ሞ/26 እና በሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ሞ/27 እንዲሁም ሁሉንም ሪፖርት ፎርሞች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካኝነት ጭምር ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

## 3. <u>መመሪያ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከ________ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ______ቀን 2011 ዓ.ም**

አህመድ ሽዴ
የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር